# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com


## የሸንጎው ከፍተኛ አመራር ምክር ቤት ስብሰባ የህዝቡን ትግል ለማጠናከር የሚያስቹሉ ተጨማሪ ውሳኔወችን በማስለላለፍ ተጠናቀቀ

ህዳር 10፣ 2007 ( ኖቨምበር 19፣ 2014)

የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) ከፍተኛ የአመራር ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን ቅዳሜ ሕዳር 6፣ 2007 ( ኖቨምበር 15፣ 2014) በተሳካ ሁኔታ አካሂዷል።

በዚህ ስብሰባ የህወሀት/ኢህአዴግ አገዛዝ በሀገራችን እና በህዝባችና ላይ እያካሄደ ያለውን ቀጣይ አሰቃቂና ህላፊነት የጎደለው ተግባሮች በዝርዝር በመመመርመር ይህ የግፍ ስርአት ተወግዶ አንድነቷ በተረጋገጠ ኢትዮጴያ ስር የሁሉም ዜጎች ሙሉ ዴሞክራሲአዊ መብት ተከብሮ፣ የህግ የበላይነት ሰፍኖ ለመኖር የሚያስችል ህገመንግስታዊ ስርአት እውን ለማድረግ የተጀመረው ትግል ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ አማራጭ የሌለው ጉዞ እንደሆነ አጽንኦት ሰጥቷል። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ፡

- ከሸንጎ የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴወች የቀረበውን የስራ አፈጻጸም ሪፖርት መርምሮ ቀጣይ የሆነ አመርቂ ስራን ለመስራት የሚያስችለውን የያንዳንዱን ኮሚቴ የስራ እቅድ አጽድቋል፡
- ሸንጎው የሀገር ቤት ትግሉን ለማጠናከር የሚያካሂደውን የተለያዩ ግንኙነት እና እርምጃ አጠናክሮ እንዲቀጥል መመሪያ ሰጥቷል።
- ባሁኑ ሰአት በሀገራችን ውስጥ የሚካሄደውን የመገናኛ ብዙሀን አፈናና በውስጥም በውጭም የሚታየውን የነጻ ሚዲያ ተግዳሮት ከተመለከተ በሏላ ይህ የሚዲያ አፈናና ሞኖፖሊ በህዝቡ ትግል ላይ ያለውን እንደምታ በማገናዘብ አማራጭ የዜና ማሰራጫ ሊጠናከርበትና ሊዳብር የሚችልበትን ጥናቶች መርምሮ በዚህ አኳያ በሸንጎው በኩል የአቅም ግንባታ ተግባሮች እና አስቸኳይ እርምጃወች እንዲወሰዱ መመሪያ ሰጥቷል፡:
- በዲፕሎማቲክ እንቅስቃሴውም እስካሁን የታዩትን አበረታች እንቅስቃሴወች ከመረመረ በሓላ በዚህ አኳያ የሚካሄደው ስራ ሁሉ በተጠናከረ መልክ በተሌያዩ የአለም ክፍሎች ተቀናጅቶ እንዲካሄድ የሚያስችል መመሪያ ሰጥቷል።
- ለ2007 በመላ ሀገሪቱ ሊካሄድ የታቀደውን ብሄራዊ ምርጫ በተመለከተም በሰላማዊ መንገድ በሀገር ውስጥ መስዋእት በመክፈል በመታገል ላይ የሚገኙት ሁሉ የገጠሟቸውን ቀጣይ ተግዳሮቶች ከመረመረ በኋላ ይህ ምርጫ ነጻና ፍትሀዊ ለመሆን እንዲችልና ለህዝባችንም የነጻነት ትግል አስተዋጽኦው ከፍ እንዲል ቀደም ሲል ያወጣውን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሀገር ቤቱን ትግል ለመደገፍና ለማጠናከር የተቀናጀና ጠንካራ እንቅስቃሴ እንዲደረግ ተጨማሪ መመሪያ ሰጥቷል።
- ሸንጎው ቁልፍ በሆኑ የሀገሪቱ ጉዳዩች ላይ በጥናት ላይ የተመረኮዘ የፖሊሲ አማራጮችን ለማቅረብ አስቸኳይ እርምጃወችን እንዲወስድ ውሳኔ አስተላላፏል፡ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ቦታ ሁሉ ቀደም ሲል አዘጋጅቶ ለህዝብ ይፋ ባደረገው አቅጣጫ (ሮድ ማፕ) ላይ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎችን ለማካሄድ የሚያስችል መመሪያ ሰጥቷል፡:
- የሸንጎውን ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ በቀጣይነት መካሄድ ያለበትን አጠቃላይ የአቅም ግንባታ ስራን በተመለከተ ሸንጎው የሚያካሂደውን ግምገማ ባስቸኳይ በማጠናቀቅ አስፈላጊ ሆነው የሚገኙ ማጠናከሪያዎችም ተግባራዊ እንዲደረጉ መመሪያ ሰጥቷል።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ